# “የታሪክ ቅሚያ ይሉታን ይህን ነው!”

## አራምባና ቆቦ (ፍየል ወዲያ ቁዝምዝም ወዲህ)

ስሙንና የሚሰራበትን ቦታ (መስሪያ ቤት) በአጠቃላይም ማንነቱን እንኳ ለመግለጽ መድፈር ያቃተው ጽሀፊ ተብየው የህወሀት ካድሬ መረጃ አልባ ስሜቱን (የህወሀት ደረቅ ፕሮፓጋንዲስትነቱን) በግልጽ ያንጸባረቀበትን ረብ የለሽ ጽሁፍ እ.አ.አ በ02/27/14 ከመቀሌ መልስ በማለት በአይጋ ፎረም ድረ-ገጽ ላይ መልቀቁ በመጽሀፋችን መልዕክት አስተላላፊነትና ተነባቢነት ላይ የሚያሳድረው አሉታዊ ተጽዕኖ ባይኖርም ለአንባቢዎቻችን ክብር ስንል የተዛባውንና ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታነት የዋለውን ጽሁፍ አንብቦ ዝም ማለት ግን እንደ ጽሀፊው ላሉ አጉል ደረቅ ፖለቲከኞች (ፕሮፓጋንዲስቶች) የማደናገሪያ ሀሳብ ቦታ እንደመስጠት ስለሚቆጠርና የዋህ (Innocent) ተደራሲያንም ዕውነታውን በአግባቡ እንዳይገነዘቡ ማድረግ ስለሚሆን የፖለቲከኛውን ግልብ አተያይ ለማጋለጥ ሲባል መልስ መስጠት አስፈልጓል፡፡

አዎ ከደራሲያኑ አንዱ የሆነው ሲሳይ መንግስቱ አዲሱም የትምክህትን ግሳንግስና የጠባቦችን በህዝብና በአገር ላይ ለመጫን የሚፈልጉትን ያልተገባ ፍላጎት ለማስቀረት የሚደረገውን ጥረት በመደገፍ በረሀ ወጥቶ ጭምር በጽናት ታግሏል፣ አሁንም ሁኔታው በሚጠይቀው አግባብ እየታገለ ይገኛል፡፡ ይህ ማለት ግን የህወሀት ካድሬዎች በራያ ህዝብ ላይ ያልተገባ ፍላጎታቸውን ሲጭኑበትና የአስተዳደር በደል ሲያደርሱበት በአይኑ እየተመለከተና በጥናትም እያረጋገጠ ባለበት ሁኔታ ዝም ብሎ መመልከት ነበረበት ካልሆነ ግን ከትምህክተኞች ጎራ አሰልፈን እንመታዋለን የሚለው ኋላ ቀርና ጸረ-ዴሞክራቲክ አስተሳሰብ ከመነሻውም የትግሉን አላማ አለማወቅና ለህዝብ መብት መከበር አለመቆምን ያሳይ ካልሆነ በስተቀር ለሀቅ መቆምን አያመለክትም፡፡

በመጀመሪያ መታየት ያለበት ጉዳይ ጽሀፊ ተብየው የህወሀት ካድሬ ደራሲያኑ ሁሉም የራያ ህዝብና አካባቢ ወደ አማራ ክልል መካተት ይኖርበታል የሚል ሀሳብ በመጽሀፋቸው ላይ አቅርበዋል የሚል መደምደሚያ ላይ መድረሱ ከመነሻው የራያ ህዝብ ያለፍላጎቱ ወደ ትግራይ መካለሉን ስለሚያውቅ የራሱን ስጋት በግልጽ ያንጸባረቀበት አገላለጽ ካልሆነ በስተቀር በመጽሀፉ ውስጥ አንድም ቦታ ላይ ሁሉም የራያ አካባቢና ህዝብ ወደ አማራ ክልል መካተት አለበት የሚል አቋም አልተንጸባረቀም፡፡ የደራሲያኑ ዕምነትና ፍላጎትም የራያ ህዝብ በየትኛውም ክልል ሆኖ አሊያም ራሱን ችሎ እንደ ክልል/ልዩ ዞን በመደራጀት ራሱን በራሱ ያስተዳድር፣ ልጆቹ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው ይማሩ ህዝቡም በሚችለው ቋንቋ የመዳኘት መብቱ ዕውቅና ያግኝና ይከበር የሚል ነው፡፡

ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ጸሀፊውን ጨምሮ ማንም ህሊና ያለው ሰው በውል እንደሚገነዘበው የራያ ህዝብ የራሱ የሆነና ለየት ያለ ማንነት ያለው ማለትም የአማራ፣ የትግራይ፣ የአገውና የኦሮሞ ብሔር-ብሔረሰብ ህዝቦች ውህድ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ ከቅርብ ጎረቤቶቹ ከትግራይና ከአማራ ብሔር ህዝቦች ሳይቀር የተለየ ባህል፣ ስነ-ልቡና፣ እምነትና ማንነት ያለው ህዝብ ስለሆነ ይኸው ልዩ ባህሪው ታውቆለት ቢያንስ ራሱን ችሎ ተደራጅቶ በራሱ ልጆች የሚተዳደርበት ሁኔታ ይመቻች የሚል ስለሆነ ነው፡፡ ፀሀፊ ተብየው የፖለቲካ ሰው ግን አብዛኛው የራያ ህዝብ እንዲመርጥ ዕድል ቢሰጠው ምን ብሎ መመለስ እንደሚችል አስቀድሞ ስለተገነዘበ የህወሀትን ያልተገባ ፍላጎት የማስጠበቅ ግልብ ፕሮፓጋንዲስትነቱን ያለሀፍረት ለማንጸባረቅ ጥረት አደረገ፡፡

ሌላው ስለወያኔ አመጽ አነሳስና አንድምታ ያለው አተያይ የተንሸዋረረ በመሆኑ የታሪክ ቅሚያ ሲል ፍየል ወዲያ ቁዝምዝም ወዲህ የሆነ ሀሳብ ማቅረቡ ነው፡፡ ለነገሩ ስለወያኔ ባህላዊ ፍልሚያና ኋላም ላይ ስለተነሳው የወያኔ አመጽ በሚገባ ለመረዳት አንድም በደንብ ማንበብን አሊያም በራያ ውስጥ ተወልዶ በራያ አባቶች ጣፋጭ የሆነውን ታሪካቸውን እየተማሩ ማደግን ይጠይቃል፡፡ ሆኖም እንዲሁ የህወሀትን ያልተገባ ፍላጎት

ለማንጸባረቅና ሲሰማው የኖረውን የቀዳማይ ወያኔን አደንቋሪ ፕሮፓጋንዳ የሚያፈርስ ሀሳብ በመረጃ ጭምር ተደግፎ በቀረበበት ሁኔታ አይኔን ግንባር ያድርገው በሚል መንፈስ የታሪክ ሽሚያ ሲል የአላዋቂ ሳሚ አይነት መረጃ አልባ የመከረካሪያ ሀሳብ አቀረበ፡፡ የሆነ ሆኖ የወያኔ አመጽ መነሻውም ሆነ መድረሻው የራያ አካባቢና ህዝብ እንደነበረ የተገነዘቡት የወቅቱ ገዥዎች የቅጣት በትራቸውን የሰነዘሩት በራያ ህዝብ ላይ እንጂ በሌሎቹ የትግራይ አካባቢ ህዝቦች ላይ ጭምር የነበረ አለመሆኑ ሲታይ እውነታውን ይበልጥ ያረጋግጣል፡፡

ይህም ሆኖ በጸሀፊው የተጠቀሱት የትግራይ አካባቢ ነዋሪዎች በአመጹ መሳተፋቸውን ጸሀፊዎቹም የዘነጉት ጉዳይ አለመሆኑን መጽሀፉን ደጋግሞ ቢያነበው ሊያረጋግጥ ይችል ነበር፣ ለእነዚህ አካባቢ ነዋሪዎች ቀጥተኛ ተሳትፎም ደራሲያኑ ዕውቅና ከመስጠታቸውም በላይ ከልብ የመነጨ አድናቆታቸውንም ይገልጻሉ፡፡ ልዩነቱ ያለው የአመጹን መነሻና የወያኔን የአመጽ እንቅስቃሴ ከራያ ቀምቶ የመላው ትግራይ መገለጫ ለማድረግ ከሚደረገው ጥረትና በስርአቱ ላይ ያኮረፉ የትግራይ ገዥ መደቦች ወደ አመጹ ከተቀላቀሉ በኋላ የአመራር ቦታውን በመጨበጥ አመጹን ለነሱ ፍላጎት ማስፈጸሚያ ለማድረግ ወደ መቀሌና አካባቢዋ ያደረጉት እንቅስቃሴ በደጃዝማች ገብረህይወት መሸሻ የተመራው የአድዋ ህዝብ አመጹን የማክሸፍ ጥረት ታክሎበት ለውድቀት የዳረጋቸው መሆኑን መገንዘብ መቻል ላይ ነው፡፡

በአመጹ መክሸፍ ሳቢያም ከላይ እንደተገለጸው የአጼ ሀይለስላሴ መንግስት የበቀል ቅጣት ሰለባ የሆነው የራያ ህዝብ እንጂ ዘግይተውም ቢሆን በአመጹ የተሳተፉት የትግራይ ገዥ መደቦችና አካባቢዎች ሁሉ እንዳልነበሩ በታሪክ የሚታወቅ እውነት ነው (በዚህ ረገድ ፕሮፌሰር ገብሩ ታረቀ የገጠሩ ህዝብ ተቃውሞ በሚል ርዕስ የጻፉትን መጽሀፍ ማንበቡ ሳይጠቅም አይቀርም)፡፡ የራያን ህዝብ ትግሬነት ለማረጋገጥ ሲባልም ከአጼ ዮሀንስ ዘመነ መንግስት ቀደም ሲል ማለትም ከ1772 ዓ.ም ጀምሮ ከአላውሀ ምላሽ እስከ ቀይ ባህር ድረስ በትግራይ ገዥዎች ማለትም በነራስ ስሁል ሚካኤልና ራስ ወልደስላሴ አገዛዝ ስር ይተዳደር ነበር ሲል የመከራከሪያ ሀሳብ ማቅረቡ ሌላው ውሀ የማያነሳ ሀሳብ ብቻ ሳይሆን በአንድ አገዛዝ ስር መቆየትና የአንድ ብሔር ህዝብ አካል መሆን ማለት እጅግ የተለያዩ ጉዳዮች መሆናቸውን በአግባቡ አለመረዳት አሊያም ሆነ ብሎ ለማምታታት መሞከር ካልሆነ በስተቀር ሌላ ትርጉም ሊሰጠው አይችልም፡፡ እንደዛ ተብሎ ከታመነም ለምን ኤርትርራን ጨምሮ የትግራይ አካል ስለሆነች አንለቅም ወይም መልሰን በግዛታችን ስር እናደርጋታለን የሚል የመከራከሪያ ሀሳብ አይነሳም? አህያ ቢራገጥ… ካልሆነ በስተቀር፡፡

በሌላ በኩል በህወሀት/ኢህአዴግ የተጠና ቀመር የተዋቀረው የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርአት በዋነኛነት ቋንቋንና የህዝብን ፍላጎት መሰረት በማድረግ ነው ስራ ላይ የዋለው እየተባለ በአደባባይ በሚለፈፍበት ወቅት ወሳኞቹ ኢህአዴግና የኢፌዴሪ መንግስት ናቸው በሚል የማንአለብኝነት አስተሳሰብ የራያ ህዝብ ሳይፈቅድና ከፊሉ የራያ ህዝብም አማርኛ፣ ኦረምኛና አገውኛ ተናጋሪ በሆነበት ሁኔታ በዛም በዚህም አምታትቶ የራስ ያልሆነን ህዝብና አካባቢ ታሪክን በማዛባት ጭምር የራስ እንደሆነ አድርጎ በማቅረብ ያለ አግባብ ለመጠቀም መሞከር አይናችሁን ጨፍኑ ላሞኛችሁ እንደማለት የሚቆጠር መሆኑ አይቀርም፡፡ ጸሀፊው ይህን የወረደና ጊዜ ያለፈበት መረጃ አልባ ብቻ ሳይሆን አመክንዮ የለሽ በደረቅ ፕሮፓጋንዳ የታጀለ ክርክሩንና ያልተገባ ፍላጎቱን በሰው ላይ ለመጫን ስለፈለገ ብቻ አለቆቹ ደጋግመው የሚጠቀሙበትን የትምክህተኛ አስተሳሰብ የተጫነው ሀሳብ ለማለት ይሞክራል (የእነሱን ጠባብ አስተሳሰብ ወደ ጎን በመተው)፡፡

የህወሀት ሰዎች ዋነኛው ችግርም ይኸው ይመስለኛል፣ ጅራፍ ራሷ ገርፋ ራሷ ትጮሀለች አይነት፣ ምክንያቱም የህወሀት ሰዎች ከነሱ ለየት ያለ ሀሳብ ይዞ የተነሳን ሁሉ አማራ ከሆነ ትምክህተኛ (ነፍጠኛ)፣ ኦሮሞ ከሆነ ጠባብ፣ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ትግሬ ከሆነ አረና የሚል ስያሜ በመስጠት ከጠላት ጎራ አሰልፈው ለማሸማቀቅ ጥረት ያደርጋሉ፡፡ በዚህ አልመለስ ካለም አስተዳደራዊ እርምጃ በመውሰድ እንቅስቃሴውን ለመግታት ይሞክራሉ (አስፈላጊ ከሆነም ወደ ከርቸሌ በማውረድ ጭምር)፣ የሚገርመው ነገር ወደ ትግራይ የተካለለው የራያ ህዝብ ሁሉም የራያን ትግርኛ ተናጋሪ እንዳልሆነ እየታወቀ (ከ70,000 በላይ የሚሆኑ አማሮች፣ ከ10,000 በላይ የሚሆኑ አገዎች እና ከ10,000 በላይ የሚሆኑ ኦሮሞዎች በራያ አካባቢ ብቻ ይገኛሉ) በትግርኛ መማራቸውና መዳኘታቸው ጸሀፊውን ጨምሮ አንዳንድ አላዋቂ ሳሚዎች ምኑ ላይ

ነው ችግሩ ሲሉ ጥያቄ ማንሳታቸው ለህጻናት መብት መከበር ምን ያህል ደንታቢስ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

ይህም ሆኖ በክልልና በዞን ደረጃ ዕውቅና አይሰጣቸው እንጂ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የራያ-አላማጣ ወረዳ አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ የሚኖርባቸው አራት ቀበሌዎችን (ከ40,000 የማያንስ ህዝብ የሚገኝባቸው) እና የራያ አዘቦ ወረዳ አማርኛ ተናጋሪ ህዝብ የሚኖርባቸው ሶስት ቀበሌዎችን (ከ30,000 የማያንስ ህዝብ የሚገኝባቸው) ለይተው እንደሁኔታው በማስተናገድ በአማርኛ ቋንቋ ለማወያየት ጥረት ማድረጋቸው ሲታይ አበረታች ጅምር መሆኑን በዚህ አጋጣሚ ለመግለጽ እንወዳለን፡፡ ይህ መረጃ ከማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲና ደራሲያኑም በአካል በአካባቢው ተገንተው ከወረዳ አስተዳደር ጽ/ቤቶች ያገኙት ስለሆነ የማያጠራጥር መሆኑን ማረጋገጥ እንፈልጋለን፡፡

ሌላው ወቅታዊ መረጃ እንኳ ይዞ ለመጻፍ አለመሞከሩ የሚያሳየው ነገር የጎንደር አካባቢ ህዝብ ድሮ ቅማንት ነበር አሁን ግን ቅማንት አልተባለም በማለት የራያን ኦሮሞዎች ህልውና አንድያውን ሊክድ መሞከሩ ነው፣ በአንድ በኩል የራያ-አዘቦና የራያ-አላማጣ ወረዳ አስተዳዳሪዎችን ቢጠይቅ የራያ ኦሮሞዎችን መኖር ያረጋግጡለት እንደነበር ቢገነዘብ ምንኛ ብልህ በሆነ፣ ሌላው ቀርቶ ራያ-አዘቦ ወረዳ ብቻ ሶስት ቀበሌዎች የራያ ኦሮሞዎች የሚኖሩባቸው እንደሆኑ ሲያክሉበት ልክ ይገባ ነበር፣ ምን ያደርጋል ከጭፍን ጥላቻ የሚነሳ ሀሳብ እንደ ወረደ ማቅረብን እንጂ የተማረው መረጃ ማገላበጥንማ ወዴት አግኝቶት? ለዚህም ነው ሰነዶች ያረጋግጣሉ ይላል እንጂ የትኞቹ ሰነዶች እንደሆኑ እንኳ መጥቀስ ያልቻለው፡፡ ለመሆኑ ቅማንቶች የማንነታችን ይከበርና ራሳችንን በራሳችን እናስተዳድር የሚል ጥያቄ አንስተው እስከ ፌዴሬሽን ምክር ቤት መድረሳቸውንስ ያውቅ ይሆን?

ከዛም አልፎ የድፍረቱ ድፍረት ደራሲያኑ ያቀረቡትን የራያን ህዝብ ማንነት ይከበርና ራሱን በራሱ ያስተዳድር ጥያቄ ሰፊው የራያ ህዝብ የሚቀበለው ሀሳብ አይደለም ሲል መደምደሙ በእርግጥም የራሱን ግልብ ስሜትና የህወሀትን የቆየ የመስፋፋት ፍላጎት ከማንጸባረቅ ያለፈ የራያን ህዝብ እውነተኛ ስሜትና ትክክለኛ ፍላጎት ለማወቅ አሁንም ዝግጁ ያልሆነ ከታሪክም ሆነ ከወቅታዊ የህዝብ እንቅስቃሴዎች የማይማር መሆኑን ነው ያረጋገጠው፡፡ ሌላው በማስረጃነት ያቀረበው ምሳሌ አላዋቂነቱን አሊያም አስመሳይነቱን ይበልጥ የሚያሳብቅበት ሆኖ አግኝተነዋል፣ ይኸውም በአበርገሌና በቦራሰለዋ ስር ለረዥም ጊዜ ሲተዳደሩ የነበሩ አገዎች እኮ ወደ ዋግ ኸምራ እንዲካለሉ ተደርጓል ሲል ህወሀት ለጋስ መሆኑን ለማስረገጥ ይሞክራል፣ እውነታው ግን ይህን አያመለክትም፣ በእነዚህ አካባቢዎች የሚገኙት አገዎች የሚኖሩበት አካባቢ በታሪክ አጋጣሚ ለምነቱን ያጣ ስለሆነና ያን ያህልም የሚያጓጓ የተፈጥሮ ሀብት ስላልነበረው ከጊዜ በኋላ ሳይቀር እነዚህን አካባቢዎች ውሰዱልን ብለው ነው እስከ መሸኘት የደረሱት፡፡

የመጽሀፉ ደራሲያን